# <u>ቻሉን ነው ፤ መቻቻል?</u>

አንዱ አንዱን ለማጥፋት ፤ ከመፈላለጉ
ምህረት ባህል ፤ ነው ያገራችን ወጉ
ክብሩ ሳይነካ ፤ ሥልጣን ማዕረጉ
የበደልን ችሎ ፤ ይቅርታ ማድረጉ ።

ጸበኛን አስታርቆ ፤ ይቅር መባባሉ
ካባት ገዳይ ታርቆ ፤ ምንም ቢበደሉ
ሰላምን ያሰፍናል ፤ ያገር ወግ ባህሉ
ጥላቻን አጥፍቶ ፤ እሳት ማቃጠሉ
ወንድማማችነት ፤ ያነግሳል መሀሉ ።

ትግል በአረና ፤
          ትግል በነ ሰዬ ፤
                    ሆኖ እርስ በርሱ
ትላንት ትላንት ቀረ ፤ እሱን አታስታውሱ
አክራሪ አትሁኑ ፤ ያለፈውን እርሱ
እያሉ መደለል ፤ ከነእርሙ ማጉረሱ
በመቻቻል ሰበብ ፤ ትፋት እየላሱ
ወሬ በማጣፈጥ ፤ ሕዝቡን እያመሱ
ያጃጅሉን ጀመር ፤ መልሰው ሊነግሡ ።

ይቅርታ እንኳን ሳይሉ ፤ ስራቸው ተረስቶ
ትግሉ በወያኔ ፤ ካድሬ ተተክቶ
ግር ግሩ በዝቷል ፤  ትግሉ ተቀምቶ
ቀደው ይጥፋሉ ፤ ያረጀ ዲሪቶ
በመቻቻል ሰበብ ፤ ቻሉን ተተክቶ ።

ትግል ተጣመመ ፤ አጓጓል ከፉኛ
ጠላት ወዳጅ ሆነ ፤ ወዳጁ ደመኛ
ወያኔን ሰባስበው ፤ ሲያሞኙን ዳግመኛ
እነሱ ሲያፈርሱ ፤ እኛ እንድንተኛ
ይለጥፉልናል ፤ ከፉውን ሥም ለኛ
ምነው ተቀለደ ፤ በትግል ግምኛ ።

መቻቻል ያባት ነው ፤ ቻሉን ግን ያዋዝል
ከታሪክ ካልተማርን ፤ ትግሉም ይጠነዛል
በጅ አዙር ወያኔን ፤ ማንገሡም ይበዛል
ጠላት አዝሎ መንገድ ፤ ወኔ ያቀዘቅዛል
አገርንም ገሎ ፤ ትውልድን ያነቅዛል ።

ትግል ላይ ነኝ ይላል ፤ ትግልን ያላየ
ወዳጅን ከጠላት ፤ ነጥሎ ያልለየ
ከአረና ትግራይ ፤ ወግኖ ከሰዬ
ባገር ይነግዳል ፤ ደም እያበራየ
ገና ጉድ ይሰማል ፤ እድሜ ሰጥቶት ላየ ።

በነ ሥም አይጠሬ ፧ ሁሉም ተኮላሽቶ
በጎጠኞች ሴራ ፧  ተፈትጎ ታሽቶ
ባድር ባይ ወላዋይ ፧ ትግሉ ተጎትቶ
የጣድነው አረረ ፧ ከሰለ ጎርንቶ
አላስቀምጥ አለ ፧ በስብሶ ቀርንቶ ፡፡

አገር ወዳድ ሁሉ ፧ ዳር እየተገፋ
ከድጡ ወደማጡ ፧ ትግሉ እየከረፋ
የዘንድሮው ይባስ ፧ ባፍጢሙ ተደፋ
ከትላንቱ ዛሬ ፧ ጭራሽ አይኑ ጠፋ ፡፡

ከሰላማዊት. አ